## ፩ መዝሙር

መዝሙር የሚለው ቃል"ዘመረ" አመሰገነ ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም ምስጋና ማለት ነው። መዝሙር በቤተ ክርስቲያን የዝማሬ ሥርዓት መሠረት በዜማ የሚቀርብ ምስጋና ነው፡፡ ምስጋና የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ እግዚአብሔር ክብሩ በባሕሪው ብቻ እንዳይቀር ስሙን እንዲቀድሱ ክብሩን እንዲወርሱ መላእክትንና ሰውን ለባውያን ማዕምራን/አስተዋይና አዋቂ/ አድርጎ ፈጥሮአቸዋል ፡፡ከቅዱሳን መላዕክት ወገን ቅሩበ መንበር አኃዜ መንጦላእት የነበረው ሳጥናኤል ያልተሰጠውን አምላክነት በመሻቱና ምስጋና እንዲቀርብለት በመፈለጉ ከክብሩ ተዋርዷል። ሕዝ.፳፰፡፲፫ በእርሱም ፈንታ እግዚአብሔርን የሚያመሰግን እጅግ ያማረና የከበረ ሰው ተፈጥሮአል። መጽሐፈ መቃብያን ሣልስ ፪፡፲፪ "እንዳንተ ካሉ ሠራዊተ መላእክት ሁሉ ይልቅ ራስህን አኩርተሃልና ስለ ትዕቢትህ እግዚአብሔር ከናቃቸው ከሰራዊቶችህ ጋር አንተ ስለምታመሰግነው ምስጋና የእግዚአብሔርን ምስጋና ያመሰግኑ ዘንድ አዳምን ከልጆቹ ጋራ ፈጠረው" በማለት የሰው ልጅ የተፈጠረበትን ዓቢይ አላማ ይገልጻል፡፡ ቅዱስ ዳዊትም "እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እባርከዋለሁ፤ምስጋናውም ዘወትር በአፌ ነው"፡፡በማለት የሰው ልጅ ያለማቋረጥና መሰልቸት ፈጣሪውን ማመስገን እንደሚገባው ተናግሯል፡፡መዝ ፴፫፤፩ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ከሰጠው ታላቅ ጸጋ መካከል የመዝሙር አገልግሎት አንዱ ነው፡፡

## መዝሙር በመጽሐፍ ቅዱስ

የመዝሙር አገልግሎት በአጋጣሚ የተጀመረ ሳይሆን ከአምላክ የተሰጠ ልዩ የአገልግሎት ጸጋ ነው፡፡የሰው ልጅ መዝሙርን የተማረው ከመላእክት ነው፡፡በመዝ፸፯፤፳፭ "የመላእክትን እንጀራ የሰው ልጅ በላ"ተብሎ የተጻፈው ቅዱሳን መላእክት የሚበሉት እንጀራ የሚጠጡት መጠጥ መኖሩን ለመግለጽ አይደለም፡፡የመላእክት እንጀራ የተባለው ምስጋናቸው ነው፡፡ቅዱሳን መላእክት ለፈጣሪያቸው የሚያቀርቡት ምስጋና ምግብ ሆኖአቸው ያለማቋረጥ ሲያመሰግኑ ይኖራሉ፡፡ "የመላእክትን እንጀራ የሰው ልጅ በላ"የሚለው አረፍተ ነገር በተለያየ ምስጢር ሊፈታ ቢችልም በተነሳንበት ዓውደ ርእስ የሰው ልጅ የመላዕክትን ምስጋና በማመስገን ከመላእክት ጋር ተባበረ በማለት እንፈታዋለን ፡፡ ይህም አነጋገር የሰው ልጅ የቅዱሳን መላእክትን ምስጋና ለማመስገን መፈጠሩን ያስረዳናል፡፡ ምንም እንኳ እንደ መላእክት እንዲያመሰግን የተፈጠረው የሰው ልጅ ንጽሐ ጠባይ ቢያድፍበትና በኃጢያት የመውደቅና የመነሣት ጠባይ ቢኖረውም በደሉን እያሰበ ይቅርታ የሚያገኝበትን ምስጋና ለፈጣሪው ከማቅረብ ፈጽሞ አልተቆጠበም፡፡በተለያዩ ዘመናት የተነሱ ሰዎች እንደተሰጣቸው ጸጋ መጠን ፈጣሪያቸውን በመዝሙር አገልግለዋል፡፡

ሕዝበ እስራኤል ከምድረ ግብፅ ባርነት ነጻ ወጥተው ባሕረ ኤርትራን በደረቅ ሲሻገሩ ይከተላቸው የነበረው ፈርኦንና ሠራዊቱ በፈረሶቻቸው ላይ እንዳሉ ባሕረ ኤርትራ ተከድኖባቸው ሲሰጥሙ ማርያም እኅተ ሙሴ ከሕዝቡ ጋር ከበሮ ይዛ "በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር እንዘምራለን...." በማለት ለፈጣሪያቸው የአንድነት ዝማሬ አቅርበዋል፡፡

ዘጸ ፲፭፥፩-፳፩ ሊቀ ነቢያት ሙሴም ለእስራኤል ልጆች በተለያዩ ጊዜያት መዝሙር ያስተምራቸው ነበር፡፡ዘዳ፴፩፤ ፴፤ ፴፪፥፩-፵፫፡፡ በእስራኤል ላይ ስትፈርድ የነበረችው ነቢይቱ ዴቦራ"… እኔ ለእግዚአብሔር እቀኛለሁ፤ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔርም እዘምራለሁ…"በማለት የዘመረችው መዝሙር ማህሌተ ዲቦራ በመባል ይታወቃል።መሳ፭፥፩-፴፩ ቅዱስ ዳዊትም በእሰራኤላውያን ዘንድ ከጥንት ጀምሮ የነበረውን የመዝሙር ሥርዓት ወስኖ ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት መዘምራንን መድቦ መዝሙሩን በተለያየ ጊዜ ከፋፍሎ እንዲዘመር ከማድረጉም በተጨማሪ ራሱም በገና እየደረደረ በቤተ መቅደስ ያገለግል ነበር፡፡ የነቢዩ ዳዊት ልጅ ጠቢቡ ሰሎሞንም ከመዝመራት ሁሉ የሚበልጥ መዝሙር "መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን" የተባለውን ዝማሬ ይዘምር ነበር፡፡

በሐዲስ ኪዳንም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ተወልዶ ባዩት ጊዜ ተለያይተው የነበሩ ሰውና መላእክት በአንድነት ዘምረዋል፡፡መዝሙር በዕለተ ሆሳዕና የቢታንያን ድንጋዮች ያዘለለ፤ጡት የሚጠቡ ህጻናትን ሳይቀር ለምስጋን ያነሳሳ ታላቅ የአገልግሎት ጸጋ ነው፡፡ቅዱሳን ሐዋርያትም ሐሙስ ማታ በአልዓዛር ቤት ቅዱስ ቁርባንን ከተቀበሉ በኃላ በአንድነት ዘምረዋል፡፡ማቴ ፳፮፤ ፴ ፡፡ በቤተክርስቲያን ትምህርት ለቅዱሳን ከሚሰጡ አስሩ ማዕረጋት ሶስተኛው ጣዕመ ዝማሬ ይባላል፡፡ከጣዕመ ዝማሬ ማዓረግ የደረሱ አበው ሳያቋርጡ ሳይሰለቹ ለፈጣሪያቸው ምስጋና ያቀርባሉ፡፡

**ራሥዋን ይፈትኑ**

1. መዝሙር ማለት ምን ማለት ነው?

2. "የመላእክትን እንጀራ የሰው ልጅ በላ" ተበሎ የተገለጸው ጥቅስ እንደ ስነጽሁፉ እንዴት ተብሎ ይፈታል?

3. ሕዝበ እስራኤል ከምድረ ግብፅ ባርነት ነጻ በወጡ ጊዜ ከሕዝቡ ጋር ከበሮ በመያዝ የዘመረችው ማን ናት?

4. ቅዱሳን ሐዋርያት ሐሙስ ማታ ቅዱስ ቁርባን ከተቀበሉ በኃላ የዘመሩት በማን ቤት ነው?

ምንጭ፤ ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ/ማኅበረ ቅዱሳን/

በቀጣዩ ጽሁፋችን መዝሙርና ጥቅሙን ለማየት እንሞክራለን